RÉPUBLIQUE FRANÇAISE
*Liberté*
*Égalité*
*Fraternité*

Santé publique France



# ስለ ማጅራት ገትር እና ሜኒንጎኮካል ሴፕሲስ

## ክትባቱን መከተብ የሚያስገኛቸው አምስት ጥቅሞች

**ዕድሜያቸው ከ11 እስከ 14 የሆኑ ህጻናት ክትባት**

ከ2023 ዓመት ጀምሮ የሜኒንጎኮካል ተስፋፊ ኢንፌክሽን ማለትም ማጅራት ገትር እና ሴፕሲስ በተለይ ከW እና Y አይነት ሜኒንጎኮካል ጋር የተያያዙ ኢንፌክሽኖች በጣም እየጨመረ መምጣቱ ተረጋግጧል። እነዚህ ኢንፌክሽኖች እጅግ ከባድ ሊሆኑ ስለሚችሉ ዕድሜያቸው ከ11 እስከ 14 ዓመት ለሆኑ ህጻናት ክትባት እንዲከተቡ ይመከራል።

## ሜኒንጎኮካል ተስፋፊ ኢንፌክሽን ሲባል ምንድ ን ነው?

በፈረንሳይ አገር ውስጥ በየዓመቱ በሜኒንጎኮካል ተስፋፊ ኢንፌክሽን የሚያዙ ሰዎች ቁጥር ከ500 እስከ 600 ይሆናል።

- ለሞት ወይም መስማት አለመቻል፣ የአእምሮ ዝግመት፣ ለአካል ማጣት መዳረግ ለሚያመጡ ተከታይ ጉዳት የሚያጋልጥ ከባድ በሽታ ነው።
- ሜኒንጎኮካል በተባለ ባክቴሪያ ምክንያት ይከሰታል። ባክቴሪያውም A፣ B፣ C፣ W እና Y የተባሉ አይነቶች አሉ። በፈረንሳይ አገር በብዛት የሚታዩት የማጅራት ገትር ባክቴሪያ B፣ W እና Y ናቸው።
- በሽታ ሳይከሰትባቸው ሜኒንጎኮካል በብዙ ሰዎች ጉሮሮ እና አፍንጫ ውስጥ የሚገኙ ባክቴሪያዎች ናቸው። በነዚህ ባክቴሪያ ከተያዙ ሰዎች ጋር በመቀራረብ፣ ለረጅም ጊዜ ወይም በተከታታይ በመገናኘት ሊተላለፉ ይችላሉ።
- በሽታው ክትባት አስገዳጅ ከሆነላቸው ጨቅላ ህጻናትም ሌላ ህጻናትን እና ወጣቶችንም ያጠቃል።
- ከA፣ C፣ W እና Y ሜኒንጎኮካል ባክቴሪያዎች የሚከላከሉ ደኅንነታቸው የተረጋገጠ ብቃት ያሳዩ ክትባቶች አሁን ላይ አሉ።

## ክትባቱ ለነማን ይመከራል?

ከዚህ በፊት የወሰዱት የሜኒንጎኮካል ክትባት ምንም አይነት ቢሆንም የሜኒንጎኮካል A፣ C፣ W እና Y ክትባት ዕድሜያቸው ከ11 እስከ 14 ዓመት ለሆኑ ህጻናት ይመከራል። ክትባቱን ላልወሰዱ ልጆች ከ14 ዓመት ጀምሮ እስከ 24 ዓመት ድረስ ክትባቱ የተመከረ ነው።

ልጆች ክትባቱን አንዴ በመውሰድ ብቻ ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት ይከካከላሉ። ክትባቱን ህጻናት ከሚወዷቸው ሌሎች ክትባቶች ማለትም የዲፍቴሪያ፣ ቴታኖስ፣ ደረቅ ሳል፣ ፖሊዮ እና ፓፒሎማቫይረስ (HPV) ክትባቶች ጋር ሊወሰዱ ይችላሉ።

## በገቢያ ላይ ስላሉት የክትባት አይነቶች በሚመለከት፤

ክትባቱን ለሚወስዱ ህጻናት Nimenrix®፣ Menquadfi ® እና Menveo® የተባሉ ሦስት አይነት ክትባትን መጠቀም ይቻላል።

## የክትባቱ የጎንዮሽ ጉዳት የትኞዎቹ ናቸው?

- ክትባቶቹን በተዋጉበት ቦታ የሰውነት ምላሽ (የሕምም ስሜት፣ መቅላት፣ እብጠት) ወይም እንደ ትኩሳት፣ ብስጭት ወይም የራስ ምታት የሆኑ ምልክቶችን ሊያስከሰቱ ይችላሉ። እነዚህ የጎንዮሽ ጉዳቶች ቀለል ያሉ እና ቶሎ የሚጠፉ ናቸው።
- እንደ ማንኛውም ክትባት እምብዛም ባይገኙም ከባድ የአለርጂክ ምላሽ ሊያስከሰቱ ይችላሉ።

## የክትባቱ ዋጋ ስንት ይሆናል ?

ከA፣ C፣ W እና Y ሜኒንጎኮካል ባክቴሪያዎች የሚከላከሉ ክትባቶች ዋጋ 65% በኢሱራንስ ማላዲ ማለትም በብሄራዊ የሕክምና መድኅን ተቋም ይሸፈናል። ቀሪው ደግሞ በሙቱኤል ማለትም በተጨማሪ የግል የሕክምና መድኅን ይሸፈናል። የCSS እና የAME ተጠቃሚዎች ግን የሚከፍሉት ገንዘብ አይኖርም።

## ክትባቱ የሚሰጠው የት ነው ?

- በኮሌዠ ትምህርት ቤቶች፤
- ክትባቱ የአጠቃላይ ሐኪሞች፣ የህጻን ሐኪሞች፣ የአዋላጅ ነርሶች፣ የአጠቃላይ ነርሶች ጋር ወይም በክትባት ማዕከሎች ውስጥ ይገኛል።

ከ2025 ዓመት የትምህርት ቤት መከፈቻ ወቅት ጀምሮ ከA፣ C፣ W እና Y ሜኒንጎኮካል ባክቴሪያ የሚከላከል ክትባት ከHPV ክትባት ጋር በአንድ ላይ በኮሌዠ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በነፃ ይቀርባሉ።

# ጥያቄ ካላችሁ ወይም ምክር ካስፈለጋችሁ ከጤና ባለ ሙያ ጋር ተነጋግሩ።

## ብቃታቸው የተረጋገጠ ክትባቶች፤

ከሜኒንጎኮካል ተስፋፊ ኢንፌክሽኖች A፥ C፥ W እና Y የሚከላከሉ ክትባቶች ከሚሰጥባቸው አገሮች የተገኙ መረጃዎች ክትባቶቹ ብቃታቸው ከፍ ያለ መሆኑን አረጋግተዋል።

## እነዚህ ክትባቶች አስፈላጊ ናቸው።

ህጻናት በሜኒንጎኮካል A፥ C፥ W እና Y የሚፈጠሩ ማጅራት ገትር እና ሴፕሲስ በመከላከል እጅግ ከባድ ሊሆኑ የሚችሉ ተከታይ ጉዳት እንዳይከሰትባቸው ያደርጋሉ።

የተከተቡ ህጻናት ከኢንፌክሽኑ ተከላክለው በሽታው ለሌላ ሰው እንዳይተላለፍ በማድረግ ክትባቱን የወሰደው ህጻን ብቻ ሳይሆን በአቅራቢያው ያሉትንም ሰዎችም ይከላከላል።

## ለመውሰድ ቀላል የሆኑ ክትባቶች፤

ህጻናት አዋቂ እስኪሆኑ ድረስ እንዲከላከላቸው አንድ ክትባት በቂ ነው። ከ10 ዓመታቸው በኋላ ከሚከተቧቸው ክትባቶች ጋር በአንድ ላይ ሊወስዱ ይችላሉ።

## አደገኝነት የሌላቸው ክትባቶች፤

የሰውነት ምላሾች አምብዛም የሌላቸው እና ቀለል ያሉ ናቸው።

## በጤና ዋስተና  የተሸፈኑ ክትባቶች፤

አሱራንስ ማላዲ የክትባቱ 65% ሸፍኖ ሙቱኤሎች ቀሪውን ይሸፈናሉ። ክትባቱ በተወሰኑ የጤና ማዕከል፥ የክትባት ማዕከል እና በኮለኽ ትምህርት ቤቶች ሊሰጥ ይችላል።

VACCINATION INFO SERVICE.FR

Le site de référence qui répond à vos questions

BAC DE TRI

DT07-505-25DE - État des connaissances : Juin 2025 – © GettyImages – AUSTRALIE - R.C.S. Paris B 378 899 363.